በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

Office of the Head of Government in
The Amhara National Regional State

ቁጥር አብክመ 11/6/7/ ርመ/17-1
Ref. No
ቀን 17 / 07/ 2013 ዓ.ም
Date

ለአብክመ ገቢዎች ቢሮ

<u>ባህር ዳር</u>

ጉዳዩ፡- **<u>በክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ ታይተው የፀደቁ አዋጆችን ስለመላክ፣</u>**

ከስመ ንብረት ዝውውር ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት በቅድሚያ መሻሻል ያለባቸው፡-

1ኛ በአብክመ የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣

2ኛ በአብክመ የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅን እንደገና ማሻሻያ አዋጅ፣

3ኛ በአብክመ የቴምብር ቀረጥ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣

እነዚህ አዋጆች በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ታይተው ወደ ህግ አውጭው ምክር ቤት የተላለፉና የአማራ በሔራዊ ክልል ምክር ቤትም በቅርቡ ከመጋቢት 2-4/2013 ዓ/ም ባካሄደው 5ኛ ዙር 6ኛ ዓመት የስራ ዘመን 17ኛ መደበኛ ጉባኤው አዋጆችን መርምሮ ያፀደቃቸው በመሆኑ እነዚህ የህግ ሰነዶች በክልሉ ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትመውና ተሰራጭተው ስራ ላይ እስኪውሉ ድረስ በክልሉ ምክር ቤት ጉባኤ ቀርበው ከፀደቁበት ከመጋቢት 4 ቀን 2013 ዓ/ም ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውሉ የተወሰነ መሆኑን እየገለጽሁ፣ ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ 3ቱም አዋጆች አባሪ ተደርገው ተያይዘው ተልከዋል።

ከሠላምታ ጋር

አገኘሁ ተሻገር ገሠሠ
ርዕሰ መስተዳድር

<u>ግልባጭ</u>

- ለም/ርዕሰ መስተዳደሩ /ያለ አባሪ/
- ለጽ/ቤቱ ኃላፊ/ያለ አባሪ/
- በጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ማዕረግ ለፕሬዝዳንቱ ዋና የህግ አማካሪ

  <u>ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት፣</u>
- ለአብክመ ክልል ምክር ቤት ጽ/ቤት

  <u>ባህር ዳር</u>

☎ + 251 058 220 0924/499
E-mail -anrsprinfo@gmail.com
✉ 312
🖷 + 251 058 220 1068/1660
website www.amharareg.gov.et

C.S "ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊነት ሁላችንም እንረባረብ"

<u>አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም</u>

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የገቢ ግብር / ማሻሻያ/ አዋጅ

<u>አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም</u>

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በክልሉ ውስጥ የታክስ ፍትሃዊነትን ለማስፈን፣ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እና የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ለማጎልበት በሥራ ላይ ያለውን የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ዓ.ም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና 3 (11) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ " **በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የገቢ ግብር /ማሻሻያ/ ዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ማሻሻያ</u>

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 240/2008 ዓ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

ሀ) የአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ተተክቷል።

ለ) ማንኛውም ሰው በክልሉ ውስጥ በሚያገኘው በማናቸውም ገቢ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

2) የአዋጁ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 7(ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 7(ሀ) ተተክቷል።

ሀ/ " **የማይንቀሳቀስ ሀብት**" ለመኖሪያ አገልግሎት የተገነባ ህንጻ ከመተላለፉ በፊት ለመኖሪያነት ያገለገለ ወይም ያላገለገለ ወይም መዋቅራዊ ፕላኑ ለመኖሪያ ሆኖ የተገነባው ጅምር ህንጻ የሚሰጠው አገልግሎት የማይታወቅን ህንጻ አይጨምርም።

3) በአዋጁ አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 7(ሐ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (መ) ተጨምሯል።

“ መ” በዚህ የማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2) በፊደል ተራ (ሀ) የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መዋቅራዊ ፕላኑ ለመኖሪያ ቤት ሆኖ ለንግድ ሥራ ሲያገለግል የቆየ ህንጻ ድርጅቱን ከዘጋበት ቀን ጀምሮ ከአንድ ዓመት በላይ ለመኖሪያ ያገለገለ ቤትን አይጨምርም፡፡

4) በአዋጁ አንቀጽ 79 ከንዑስ አንቀጽ 1(ረ) ቀጥሎ የተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሰ) ተጨምሯል፡

“ ሰ” በአዋጁ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር “ረ” ስር የተደነገገው ቢኖርም የግዥ ደረሰኝ የማይገኝላቸው የንግድ ዘርፎች በሚሸጡት ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ላይ በተወሰነ ምጣኔ ወጪያቸው ሊያዝላቸው ይችላል ፡፡የንግድ ዘርፎችን እና የወጪ መጣኔውን በሚመለከት በገንዘብ ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ዝርዝር መመሪያ ይወጣል፡፡

3. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ የማሻሻያ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ከስመ ንብረት ዝውውር ጋር ተያይዞ በእንጥልጥል ላይ ያሉ እና ስመ ንብረት ዝውውር ያልተከናወነባቸው ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

4. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ካጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

------- ቀን 2013 ዓ.ም

አገኘሁ ተሻገር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዘዳንት

__አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም__

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

__አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም__

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅን እንደገና ማሻሻያ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሥራ ላይ ያለውን የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) በድጋሜ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና 3(11) ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

1. __አጭር ርዕስ__

ይህ አዋጅ " **በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የተርን ኦቨር ታክስ / እንደገና ማሻሻያ / አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. __ማሻሻያ__

የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 83/1995 ዓ.ም. እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ በድጋሜ ተሻሽሏል።

1) የአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ተተክቷል።

ሀ/ ለመኖሪያ አገልግሎት የተገነባ ህንጻ ከመተላለፉ በፊት ለመኖሪያነት ያገለገለ ወይም ያላገለገለ ወይም መዋቅራዊ ፕላኑ ለመኖሪያ ሆኖ የተገነባው ጅምር ህንጻ የሚሰጠው አገልግሎት የማይታወቅን ህንጻ ሽያጭ

2) በአዋጁ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 7(ኀ) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (ነ) ተጨምሯል፡፡

ነ) መዋቅራዊ ፕላኑ ለመኖሪያ ቤት ሆኖ ለንግድ ሥራ ሲያገለግል የቆየ ህንጻ ድርጅቱን ከዘጋበት ቀን ጀምሮ ከ1 ዓመት በላይ ያገለገለ ህንጻ ሽያጭ

3. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ የማሻሻያ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ከስመ ንብረት ዝውውር ጋር ተያይዞ በእንጥልጥል ላይ ያሉ እና ስመ ንብረት ዝውውር ያልተከናወነባቸው ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

4. <u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ የክልሉ ምክር ቤት ካጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

------- ቀን 2013 ዓ.ም

አገኘሁ ተሻገር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዘዳንት

አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የቴምብር ቀረጥ / ማሻሻያ / አዋጅ

አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴምብር ቀረጥ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በሥራ ላይ ያለውን የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 31/1991 ዓ.ም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ስለቴምብር ቀረጥ አዋጅ በተለያየ ጊዜ ማሻሻያ የተደረገባቸውን አዋጆች ለአፈፃፀም እንዲያመች በአንድ ማጠቃለል በማስፈለጉ፣

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) እና 3 (11) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ " **በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሰት የቴምብር ቀረጥ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ----/2013 ዓ.ም** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

1. የቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 192/2003 እና 249/2009 የነበሩ ድንጋጌዎች በዚህ ማሻሻያ አዋጅ ተጠቃለው እንዲካተቱ ተደርገዋል
2. ስለ ቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 31/1991 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፡፡

ሀ/ በአዋጁ ውስጥ አግባብ ባላቸዉ ድንጋጌዎች ዉስጥ “ገንዘብ ቢሮ” የሚለው ስያሜ ተሰርዞ “የገቢዎች ቢሮ” ወይም /ቢሮው/ በሚል ተተክቷል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

(ለ) የአዋጁ አንቀጽ 3 መንደርደሪያ ራሱን ችሎ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተደረገና በስሩ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ ንዑስ አንቀጽ (12) ሆነው የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ደግሞ ከፊደል ተራቁጥር (ሀ) እስከፊደል ተራ ቁጥር (ቸ) ሆነው ከተስተካከሉ በኋላ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ከተራ ፊደል "ነ" እስከ "አ"ሆኖ ተካቷል እንዲሁም አዲስ ንዑስ አንቀፅ (2) በተጨማሪነት እንዲካተት ተደርጓል፡-

ነ) በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ሀብት የሚወርሱ ወራሾች የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ዋጋ ላይ 1% ብቻ ይሆናል፡፡

ኘ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወራሾች በሞግዚት እንዲተዳደር ሆኖ ከቆዩ በኋላ ወራሾች የድርሻቸውን ንብረት ሲከፋፈሉ ከአሁን በፊት ለስመ ንብረት ዝውውር የከፈሉበት ማስረጃ ከቀረበ በድጋሜ የቴምብር ቀረጥ አይጠየቅበትም፡፡

አ) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የግለሰብ ስም መጠሪያ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲቀየር ከተደረገ እና በህግ አስገዳጅነትት የግለሰብ መጠሪያ ስሙ መቀየሩን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ከተቻለ የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ዋጋ ላይ 1% ብቻ ይሆናል፡፡

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ቁጥር (ቸ) ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በሞት ወይም በሌሎች የፍቺ ምክንያቶች የሁለቱ ተጋቢዎች የጋራ ሀብት የሆነ ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ከአንደኛው ተጋቢ ወደ ሌላኛው ስም በሚተላለፍበት ጊዜ ለሚፈፀም የስመ-ንብረት ዝውውር የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም፡፡

ሐ) የአዋጁ አንቀጽ 9 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 9 ተተክቷል፣

9. **ቅሬታ የማቀረብ መብት**

የገቢዎች ቢሮ በወሰነው የቴምብር ቀረጥ መጠን ላይ የማይስማማ ማንኛውም የቴምብር ቀረጥ ከፋይ ቢሮው ውሳኔውን በጽሑፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ከሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

መ/ ከአዋጁ አንቀጽ 9 ቀጥሎ የሚከተለት አዳዲስ አንቀጾች 10 እና 11 ተጨምረዋል፡፡

10/.ለግብር ይግባኝ ጉባኤ ስለሚቀርብ ይግባኝ

1/ በማንኛውም የቴምብር ቀረጥ አወሳሰን ቅር የተሰኘ ግብር ከፋይ ይግባኙን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚቀርብ ይግባኝ፡-

ሀ/ ቀረጥ ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የቴምብር ቀረጥ መጠን ሃምሳ በመቶ ለቢሮው ካስያዘ፣ እና

ለ/ የቀረጥ ውሳኔ ማስታወቂያው ወይም በአቤቱታ አጣሪ ቡድን የተሰጠው ውሳኔ ለቴምብር ቀረጥ ከፋዩ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ካላቀረበ በግብር ይግባኝ ጉባዔው ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) "ሀ"እና "ለ" የተደነነጉት እንደተጠበቀ ሆኖ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ዓ.ም ውስጥ በታክስ ውሳኔ ስለሚቀርብ ቅሬታ ወይም ስለይግባኝ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በዚህ መሠረት ለሚቀርበው ቅሬታ ወይም ይግባኝ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

11 **የግብር ይግባኝ ጉባኤ ውሳኔን በመቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1. የግብር የይግባኝ ጉባኤ የሰጠው ውሳኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የግብር ይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡
2. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሕግ ረገድ የተነሳውን ክርክር መርምሮየይግብኝ ሰሚውን ውሳኔ በመሻር ወይም በማፅናት ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ጉባኤው /ለቢሮው/ ሊመልሰው ይችላል፡፡
3. በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔው በተሰጠው በ30 ቀን ውስጥ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

ሠ) የአዋጁ አንቀጽ 14 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 14 ተተክቷል፡፡

14. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

(1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

(2) የክልሉ ገቢዎች ቢሮ ይህንን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

15. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ የማሻሻያ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ከስመ ንብረት ዝውውር ጋር ተያይዞ በእንጥልጥል ላይ ያሉ እና ስመ ንብረት ዝውውር ያልተከናወነባቸው ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሰረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡

16. **ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

1. ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ህግ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
2. የቴምብር ቀረጥ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 192/2003 እና 249/2009 በዚህ ማሻሻያ ዋጅ የተጠቃለሉ ስለሆነ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

ረ/ ከአዋጁ አንቀጽ 14 ቀጥሎ የሚከተሉት አዳዲስ አንቀጾች 15 እና 16 የገቡ ሲሆን በነዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌዎች መካተት ምክንያት አንቀጽ 15 የነበረው አንቀጽ 17 ሆኖ ወደፊት ተሸጋሽጓል፡-

ሰ/ የአዋጁ የቀድሞ አንቀጽ 10፣11፣12፣13፣ 14 እና 15 አንቀጽ 12፣13፣14፣15፣ 16 እና 17 ሆነው ተሸጋሽገዋል፡፡

3. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ቀን</u>**

ይህ አዋጅ የክልሉ ምክር ቤት ካጸደቀበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

------- ቀን 2013 ዓ.ም

አገኘሁ ተሻገር

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዘዳንት